# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2015/07

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ መንግሥት ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን አከበረ

**አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤የካቲት 26 ቀን 2007 ዓ.ም.:-** የአሜሪካ መንግሥት በዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲው በኩል በየዓመቱ በዚህ ቀን ታስቦ የሚውለውን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር "ለተግባራዊነቱ እንትጋ!" በሚል መሪ ቃል በዛሬው ዕለት አከበረ፡፡ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን መከበር የጀመረው የዛሬ 100 ዓመት ገደማ ሲሆን፤ ዕለቱ የሴቶችና የልጃገረዶች ስኬቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወሳበት ነው፡፡

በዚህ የህይወት ልምድ ልውውጥ ላይ ባተኮረውና በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ስኬታማ የዩኒቨርሲቲ ህይወት የተሰኘ መርሀ ግብር ድጋፍ በተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ፤ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክና ሌሎች በተለያዩ መስኮች አርአያ የሆኑ ሴቶች ተገኝተው ከ100 በላይ ለሚሆኑ የዩኒቨርሲቲው ሴት ተማሪዎችና ሠራተኞች የህይወት ልምዳቸውን አካፍለዋል፡፡ የመድረኩ ዓላማ ሴት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ተግተው እንዲሠሩና ዓላማቸውንና ትልማቸውን ለማሳካት እንዲነሳሱ ማድረግ ነው፡፡

አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክ ለተማሪዎቹ ንግግር ባደረጉበት ወቅት፡- "እነዚህን የዛሬዎቹን ወጣት ታዳሚዎቻችንን ስመለከት የነገዎቹን ባለሀብቶች፣ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮች፣ እናቶች፣ ለተተኪው ትውልድ አርአያ ሆነው በክትትል የሚያበቁ ሴቶችን አያለሁ፡፡ እናንተ በምታደርጉት አስተዋጽኦም፤ ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ በትክክለኛው መንገድ ላይ ትገኛለች፤የኢትዮጵያ ሴቶችም የዕድሜ ጣሪያ ከፍ ይላል፡፡ ሴቶች በንግዱም ሆነ በግብርናው ዘርፍ ስኬታማ ይሆናሉ፤የኢትዮጵያ ሴቶችም በትምህርት የላቁ ይሆናሉ፡፡ የዛሬዎቹ ወጣት ሴቶችም የነገይቱን ኢትዮጵያ እንደምትገነቡ በመተማመን ለተግባራዊነቱ ትተጉ ዘንድ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ" ብለዋል፡፡

በፋሚሊ ሄልዝ ኢንተርናሽናል 360 የሚተገበረው ስኬታማ የዩኒቨርሲቲ ህይወት የተሰኘው መርሀ ግብር ዓላማው ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገቡ ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡና ትምህርታቸውን በሥርዓቱ አጠናቀው መመረቅ እንዲችሉ የዩኒቨርሲቲዎቹን አቅም በማጠናከር ረገድ ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡ እስካሁን በህይወት ክህሎቶች ሥልጠና፣በእንግሊዝኛ ቋንቋ፤ በክትትልና ድጋፍ ከ2,250 በላይ ሴት ተማሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት ለልጃገረዶችና ለወጣት ሴቶች የትምህርትን ተደራሽነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጥረት በማድረጉ የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ጨምሯል፡፡ ይሁንና በየዩኒቨርሲቲው በሚንፀባረቁ ለሴት ተማሪዎች አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎችና የአገልግሎቶች ውስንነት የተነሳ አሁንም የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶቹ ጋር ሲነፃፀር

በየጊዜው በማሽቆልቆል ላይ ያለና ሴት ተማሪዎች ከወንድ አቻዎቻቸው በበለጠ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

ስኬታማ የዩኒቨርሲቲ ህይወት የተሰኘው መርሀ ግብር በተሳካ ሁኔታ ሊተገበር የቻለው በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲና በትምህርት ሚኒስቴር ቅንጅት፤እንዲሁም የሴቶች የህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ብሪትሽ ካውንስል፣የአሜሪካ የሰላም ጓዶች፣ የሦስት አጋር ዩኒቨርሲቲዎች ማለትም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ባደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ነው፡፡

###